# ተንሥአት እሙታን፡ ማርያም ድንግል!
# ከመ ትንሣኤ ወልዳ ዘልዑል!

## ማርያም ድንግል፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች!
## በሉዓላዊው የልጇ ትንሣኤ፡ እርሱን መሰለች!

\+ + +

***ልዑል እግዚአብሔር፡***
***እንኳን፡***

**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በግርማ መለኮቱ ተገልጸ የታየበትን፡**
**የደብረ ታቦርን በዓል፥**
**እንዲሁም፡**
***ሃይማኖታችንና አገራችን፥ እናታችንና ንግሥታችን፡***
**ቅድስት ድንግል ማርያም፡**
**ከሙታን ተለይታ የተነሣችበትን፡ የትንሣኤዋን በዓል፡**
**ዘንድሮም፡ በኹለት ሺ ኹለተኛው ዓመተ ምሕረት፡**

**በያለንበት፡ በደኅና አድርሶ፡ በሰላም ለማክበር አበቃን!**

\+ + +

# የደብረ ታቦር (ቡሔ) በዓል፡

ለእኛ ለኢትዮጵያውያን: ከታላላቅ በዓሎቻችን: አንዱ የኾነው: ***በዓለ ደብረ ታቦር*** የሚውለው: በነሓሴ ፲፫ ቀን በመኾኑ: ለጾመ ፍልሰታ ሱባዔ ልዩ ምዕራፍ ኾኖ: በታላቅ መንፈሳዊ ተመስጦና ማኅሌት ይከበራል::

ይህ በዓል: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: በዓጸደ ሥጋ አብረውት ከነበሩት ደቀ መዛሙርቱ መካከል: ጴጥሮስንና ያዕቆብን÷ ወንድሙንም ዮሓንስን÷ በዓጸደ ነፍስ ካሉት ባለሟሎቹ ደግሞ: ሙሴንና ኤልያስን: ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ በሚገኘው: "ታቦር" በተባለው የወይራ ዛፍ ተራራ ላይ አምጥቶ: የባሕርይ አምላክነቱን በመግለጥ: ታማኞች አገልጋዮቹ: ሊያዩ የተመኙትን: እንዲያዩ÷ ሊሰሙ የተመኙትንም: እንዲሰሙ ያደረገበት ቸርነቱና ኃይሉ የሚዘከርበት ነው::

ይህንም: እርሱ: ለሕዝቡ: በምሳሌ ያስተምራቸው የነበረው: ነቢዩ ኢሳይያስ: "**እያዩ: ስለማያዩ÷ እየሰሙም ስለማይሰሙ÷ ስለማያስተውሉትም**" ወገኖች: የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መኾኑን: ጌታችን: ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ: መልስ በመስጠት ያስረዳቸው ቃሉ: በሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት ላይ ዘወትር ይወሳል፤ ይህም: "**የእናንተ ግን: ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ÷ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ: ብፁዓን ናቸው:: እውነት እላችኋለሁ! ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን: የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው: አላዩም፤ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው: አልሰሙም::**" ሲል: ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ነው::

በዚያ የታቦር ተራራ ላይ የታየውንም ተአምራት: እንዲህ የሚለው: የምሥራቹ ዜና አጠቃልሎ ይገልጸዋል:-

**ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ: "ጴጥሮስንና ዮሓንስን÷ ያዕቆብንም ይዞ: ሊጸልይ: ወደተራራ ወጣ:: ሲጸልይም: የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም: ተብለጭልጮ: ነጭ ኾነ:: እነሆም: ኹለት ሰዎች: እነርሱም: ሙሴና ኤልያስ: ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ በክብርም ታይተው: በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው: ስለመውጣቱ ይናገሩ ነበር::**

**"ነገር ግን: ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት: እንቅልፍ ከበደባቸው፤ ነቅተው ግን: ክብሩንና ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩትን ኹለት ሰዎች አዩ:: ከእርሱም ሲለዩ: ጴጥሮስ: ኢየሱስን: 'አቤቱ÷ በዚህ መኾን: ለእኛ: መልካም ነውና: አንድ: ለአንተ÷ አንድ: ለሙሴ÷ አንድ: ለኤልያስ: ሦስት ዳሦችን እንሥራ!' አለው፤ የሚናገረውንም አያውቅም ነበር::**

**"ይህንም ሲናገር: ደመና መጣና ጋረዳቸው፤ ወደደመናው ሲገቡ ሣሉም: ፈሩ:: ከደመናውም: "የመረጥሁት ልጄ: ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት!" የሚል ድምፅ መጣ:: ድምፁም ከመጣ በኋላ: ኢየሱስ: ብቻውን ኾኖ ተገኘ:: እነርሱም: ዝም አሉ፤ ካዩትም ነገር: በዚያ ወራት: ምንም÷ ለማንም አልተናገሩም::"** (ማቴ. ፲፫÷ ፲፫-፲፯:: ሉቃ. ፱÷ ፳፰-፴፮::)

## ቡሔ።

የደብረ ታቦር በዓል፡ በሕዝባዊው ዘይቤ፡ "ቡሔ" ተብሎ ይከበራል። በበዓሉ ዋዜማ፡ በየቤቱ፡ ችቦ ከበራ በኋላ፡ ከሠርክ ጀምሮ፡ በምሽቱ ጊዜ፡ ወጣቶች ወንዶች ልጆች፡ በየሠፈራቸው፡ በቡድን፡ በቡድን እየኾኑና በትር በትራቸውን ይዘው፥ ጅራፍ ሠርተው እያጮሁ፥ ለበዓሉ የተለመደውንም፡ "ቡሔ በሉ! ሆ! ልጆች ኹሉ! ሆ! እዚያ ማዶ፡ ጭስ ይጨሳል! አጋፋሪ፡ ይደግሣል! ያንን ድግሥ፡ ውጬ ውጬ! በድንክ አልጋ፡ ተገልብጬ! ያች ድንክ፡ ዓመለኛ! አላንድ ሰው፡ አታስተኛ!" የሚለውን የጭፈራ ሆታ፡ በመቀባበል እያሰሙ፡ "እንኳን አደረሳችሁ!" ለማለት፡ በመንደራቸው መኖሪያ ቤቶች ኹሉ ይዘዋወራሉ።

በየገቡበት ቤትም፡ ዙሪያውን ከብበው፥ በበትራቸው ወለሉን እየደቁና ከአንዱ የሆታ አውራጅ ጓደኛቸው፡ "ሆያ ሆዬ! ሆ! የኔ ጌታ! የሰጠኝ ሙክት! መስከረም ጠባ! ያንን ሳነክት! …"ሆያ ሆዬ! ሆ! የኔ እመቤት! የፈተለችው! የሸረሪት ድር! ያስመሰለችው! …" የሚለውን የሆታ ዜማ እየተቀባበሉ፡ የቤቱን አባወራና እመቤት ያሞግሳሉ። ባለቤቶቹም፡ "እንኳን አብሮ አደረሰን! ደግሞም፡ ለከርሞ (ለሚመጣው ዓመት)፡ እንዲሁ፡ በሰላም ያድርሰን! የዘንድሮውም፡ የቡሔ ዳቧችሁ ይኸውላችሁ!" ብለው፡ ትኩሱን ሙልሙል የቡሔ ኅብስት አበርክተውላቸውና መርቀዋቸው ያሰናብቷቸዋል። ልጆቹም፡ ያንን ምርቃትና የቡሔ ዳቦ ተቀብለው፡ "ዓመት ዐውደ ዓመት፡ ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! የጌታዬ ቤት! ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! የእመቤቴ ቤት! ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! እንደዚሁ እንዳላችሁ! ሆ! አይለያችሁ!" እያሉ መልካም ምኞታቸውን በመግለጽ እጅ እየነሡ ይወጣሉ።

"ቡሔ" ማለት፡ "ቡሔዬ"፥ ብርሃኔ፥ መብራቴ ማለት ነው፤ በደብረ ታቦር፡ እንደመብረቅ የብልጭታ ብርሃን፡ ቧ ብሎ የተገለጠውን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የፊቱን ጸዳል፥ የልብሱንም እንደበረዶ ነጭ መኾን ያስረዳል፤ የችቦው መብራት ምሳሌ፡ ይህ ነው። ደግሞም፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ለከት" ማለት፡ "ታናሽና ሞላላ፡ የሊጥ መፈተኛ፥ ጢብኛ፥ የዳቦ እንጎቻ" ማለት ሲኾን፡ እረኞች፡ "አክሥቴ ቤት፡ አለኝ ለከት!" ከሚሉት ሙልሙል የተነሣ፡ "ቡሔ"፡ በግእዝ፡ "ብሑእየ"፡ ማለትም፡ "ቡሖዬ" ተብሎ ስለሚተረጐም፡ የደብረ ታቦር በዓል ዕለት፡ ተቦክቶ የሚጋገረውን ኅብስት ያሳያል፤ ስለዚህ፡ "የቡሔ ዳቦ" የሚባለው ኅብስት፡ ባሕርየ መለኮቱ፡ በደብረ ታቦር የገለጠው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ መኾኑን ማስተዋል ይገባል። (**ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ደ.ተ.ወ. ገጽ. ፪፷፩።**)

በዘመነ ብሉይ፡ ሙሴ፡ ከባለሟልነቱ የተነሣ፡ አምላኩ እግዚአብሔር፡ "እባክህ፡ **ፊትህን (ክብርህን) አሳየኝ!**" ባለው ጊዜ፡ የሰጠው የተስፋ መልስ፡ "**ሰው፡ አይቶኝ አይድንምና፡ ዛሬ፡ ፊቴን ማየት አይቻልህም፤ የምታይበት ጊዜ ግን ይመጣል!**" የሚል ነበረ።

ያ፡ የተስፋ ቃል ተፈጽሞለት፡ ሙሴ፡ በዚያ ጥያቄው ጊዜ፡ በመለኮትነቱ ባሕርይ ግርማ ሊያየው ያልቻለውን፥ በኋላ ዘመንም፡ "ይህ ሥጋዬ ነው፤ ብሉት!" ብሎ፡ ራሱን፡ ኅብስት አድርጎ ያቀረበውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ገዝፎ ሊያየው ችሏል።

የቤተ ክህነታችን ምሁራን፡ በዚህ ረገድ፡ "ገራህተ ሙሴ አንቲ ነሽ!" በሚለው፡ በማግሰኞው ውዳሴ ማርያም ትርጓሜያቸው የሚሰጡትን ሐተታ፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ አግባብ ይኾናል፤ ይህም፡ እንዲህ የሚል ነው፦

*"ሙሴ፡ ከባለሟልነቱ የተነሣ፡* [ቃሉን እያሰማ የሚያነጋግረውን እግዚአብሔርን፡] *'ባይህ እወድዳለሁ!' አለው።*

*እግዚአብሔርም፡ 'የእኔን ፊት አይቶ፡ አንድ ሰዓት መቆም፥ መቆየት የሚቻለው የለም!' አለው።*

*ሙሴም፡'ካላየሁህማ፡ ለምን፡ ባለሟልህ ተባልሁ?' አለው።*

እግዚአብሔርም፡ *'ፊቴን፡ ከኋላዬ እንጂ፡ ከፊትለፊት አላሳይህም!'* [ይህም ማለት፡] *ዘር ካልወደቀባት ምድር የበቀለ ስንዴን አምጥተህ ብትሠዋልኝ፡ እታይሃለሁ!' አለው።*

*ሙሴ ማለት፡ የዋህ ማለት ነው፡ ለጊዜው በራእይ ሲባክን አድሩዋል፤ ፍጻሜው ግን፡ 'ለ[ሰብአዊ] ዘር ከተወለደች፡ ከድንግል፡ ያለ[ሰብአዊ] ዘር ተወልጄ፡ ኋላ፡ በደብረ ታቦር፡ መሥዋዕት ኾኜ በምቀርብበት ጊዜ፡ እታይሃለሁ!' ሲል ነው። መምህር ኤስድሮስ ግን፡* [ሙሴ፡ በዐፈር የተሞላ]*የብረት መደብ አሠርቶ፡ ውኃ እያጠጣ፡ አሸክሞ፡ ዐርባ ዘመን ዙርዋል!' ብለዋል።"*

እንግዲህ፡ ዛሬ፡ በደብረ ታቦር በዓል ዕለት (በቡሔ) ምሽት፡ "የቡሔ ዳቦ" ተብሎ፡ ለሕፃናትና ለወጣቶች፥ ለጎልማሶችም የሚበረከተው ኅብስት፡ የዚህ ምሳሌ ነው።

የወንዶቹ ልጆች የሆታ ጭፈራ የሚያዘክረው፡ ከደስታውና ከድንጋጤው የተነሣ፡ *"የሚያደርገውን አያውቅም ነበር!"* የተባለውን፡ የቅዱስ ጴጥሮስንና የቀሩትን የኹለቱን ሐዋርያት አድራጎት ሲኾን፥ የችቦው መብራትና የጅራፉ ጩኸት ደግሞ፡ በዚያን ተራራ ላይ፡ ከጋረዳቸው ደመና ውስጥ ብርሃነ መለኮቱን ለመግለጽ ከታየው መብረቃዊ የብልጭልጭታ ብርሃን ጋር ለተሰማው ነጐድጓዳዊ የመለኮት ድምፅ ምሳሌ ነው። (ዘጸ. ፴፫፥ ፲፪-፳፫። ማር. ፱፥ ፪-፰።)

# በዓለ ፍልሰታ ለማርያም
# እና
# ሰማያዊ ልዕልናው፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ በዓመቱ ውስጥ ከምንጾማቸው፡ ከሰባቱ አጽዋማታችን መካከል፡ ፯ተኛዋ የኾነችውን፡ "ጾመ ፍልሰታ"ን፡ ለኹለት ሳምታት በሚዘልቅ ሱባኤ፡ ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፭ ቀን ድረስ ከጾምናት በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በነሐሴ ፲፮ ቀን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ትንሣኤዋን እናከብራለን፡፡

ይህ የትንሣኤዋ ዕለት፡ ሓዋርያት፡ ወደሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው ኼደው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና ማየታቸው፥ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እርሷን፡ እናቱን፡ መንበር፥ ራሱን፡ ሠራዒ ቄስ፥ ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስን፡ ረዳት ካህን፥ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፡ ራሱንና እርሷን፥ እነርሱንም ያቆረበበት ታላቅ በዓላችን ነው፡፡

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ዜና መዋዕሏ፡ በተለይም፡ የዕረፍቷ፥ የትንሣኤዋና የዕርገቷ ዜና፡ በይበልጥ ሊነገርና ሊሰማ የሚገባው፡ በዚህ ቀን ስለኾነ፡ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡-

ቀድሞ፡ በሥነ ፍጥረት፥ ኋላም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ፡ ብዛታቸው ሊቆጠር የማይቻል፡ መልካካም ነገሮችን ላበረከተልን ፈጣሪያችን፡ ለእግዚአብሔር እንደምናደርገው ኹሉ፥ "እመቤታችንና ኪዳናችን፥ ሃይማኖታችንና መቅደሳችን፥ አገራችንና እናታችን፥ ንግሥታችንም" ስለኾነችው፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያምም፡ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በየሕሊናችን የምናስበው፥ በአንደበታችን የምንናገረውና በየሕዋሳታችን የምንፈጽመውም ኹሉ፡ በየሕይወታችን ውስጥ፡ አብሮን ሕያው ኾኖ ለዘወትር ባለማቋረጥ የሚካኼድ እንጂ፡ በአንድ ቀን ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡

አኹንም፡ እዚህ ላይ አቅርበን የምናሰማችሁ ዜና መዋዕሏ፡ በተለይ፡ በአዲስ ኪዳኑ መጽሓፍ ውስጥ ተመዝግቦ የሚነበበውን፥ ልጇ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስካረገበትና መንፈስ ቅዱስ፡ በሓዋርያት ላይ እስከወረደበት ቀን ድረስ ያለውን ሳይኾን፡ ከዚያ በኋላ፡ በዚያው መልክና ይዘት የቀጠለው ምድራዊ ሕይወቷ፡ በ፷፬ ዓመታት ዕድሜዋ ካበቃበት፡ ከዕረፍቷና ከፍልሰቷ ቀን ተነሥተን፡ የመጨረሻ የኾነውን፡ የትንሣኤዋንና የዕርገቷን ዜና ብቻ ይኾናል፤ እርሱም፡ የዕረፍተ ሥጋዋንና የፍልሰቷን በዓል በምናከብርባት፡ በጥር ፳፩ ቀን፡ እንዲህ በሚለው ቃል ይገለጻል፡፡

የእመቤታችን ሥጋዊ ዕረፍቷና ፍልሰቷ፡ ጥር ፳፩ ቀን፡ በዕለተ እሑድ ነው፡፡ ፲፪ቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ሓዋርያት፡ የዕረፍቷን ቀን፡ ቀደም ብለው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው፡ በሙሉ፡ በአጠገቧ ተሰባስበው ስለነበረ፡ የመጨረሻ ቃሏን አሰምታቸውና በረከቷን አሳድራባቸው፡ በሰላም አንቀላፋች፤ ቅድስት ነፍሷ፡ ከቅዱስ ሥጋዋ ተለየች፡፡ እነርሱም፡ ቅዱስ ሥጋዋን፡ በአጎበር አድርገው፡ ሊቀብሩ፡ ወደጌቴሴማኒ ተሸክመው ሲኼዱ፡ አይሁድ፡ እንደልማዳቸው፡ "ቀድሞ፡ ልጇን፡ 'ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! ዓረገ!' እያሉ፡ ሲያውኩን ይኖራሉ፤ ዛሬ ደግሞ፡ እርሷን፡ እንዲሁ 'ተነሣች! ዓረገች!' እያሉ ሊያውኩን አይደለምን? ኑ! በእሳት እናቃጥላት!" ብለው፡ ዐድመው ተነሡ፡፡ ከእነርሱ መካከል አንዱ፡ "ታውፋንያ" የሚባለው አይሁዳዊ፡ ተራምዶ፡ አስከሬኗ ያረፈበትን የአልጋውን አጎበር ጨበጠው፡፡ ወዲያው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ኹለቱንም እጆቹን ቀጣው! እጆቹም፡ በአጎበሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ!

ታውፋንያ፡ ሳያስበው፡ ድንገት በደረሰበት፡ በዚህ ጽኑ መቅሠፍት እጅግ ተደናግጦ፡ እዚያው በወደቀበት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመነ÷ "የእውነተኛው አምላክ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፡ አንቺ፡ በእውነት፡ ድንግል ነሽ! ስለዚህ፡ እኔ በደለኛውን፡ ይቅር ትዪኝ ዘንድ፡ እለምንሻለሁ!" ሲል፡ የልመና ጸሎቱን፡ በልቅሶና በዕንባ፡ ወደእመቤታችን ስላቀረበም÷ በሓዋርያትም ምልጃ፡ እጆቹ ወደነበሩበት አካሉ ተመልሰውለት፡ ደኅና ኾነ፡፡

ከዚህ በኋላ፡ መልአኩ፡ ሓዋርያው ዮሓንስን ጨምሮ፡ የእመቤታችንን ቅዱስ ሥጋ፡ በደመና ነጥቆ፡ ወደገነት ወሰደው፤ እዚያም፡ በዕፀ ሕይወት ሥር አኖረው፡፡ ኋላ፡ ሓዋርያት፡ ዮሓንስን ሲያገኙት፡ "እመቤታችን እንደምን ኾነች?" አሉት፡፡ እርሱም፡ "በገነት፡ ከዕፀ ሕይወት ሥር ዐርፋለች!" አላቸው፡፡ [የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘች፡ ራሷ፡ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት ስትኾን፡ "በራሷ ሥር ዐረፈች!" ማለት፡ ምሥጢሩ፡ እጅግ ጥልቅ ስለኾነ፡ በአንክሮና በተመስጦ ያጠያይቃል። ]

የቀሩት ሓዋርያት፡ "ዮሓንስ፡ ድንቅ የኾነውን፡ ያን፡የእግዚአብሔር ሥራ አይቶ፡ እኛስ፡ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን!? አቤቱ÷ ለእኛም ቸርነትህን አድርግልን!" ብለው፡ በነሓሴ መባቻ (መግቢያ= ፩ ቀን)፡ በአንድነት ኾነው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ የሱባኤ (የ፩ ሳምንት) ጾምንና ጸሎትን ጀመሩ፡፡ በኹለተኛው ሱባኤ ማብቂያ ዕለት፡ ነሓሴ ፲፬ ቀን እሑድ፡ የእመቤታችንን ቅዱስ ሥጋ፡ ሙቀቱ እንዳለ ትኩስ እንደኾነ፡ መልአኩ፡ ከገነት አምጥቶ፡ ለሓዋርያት ሰጣቸው፡፡ እነርሱም፡ ልመናቸው ስለተፈጸመላቸው፡ ፈጣሪያቸውን፡ በጸሎት አመስግነው፡ በዚያችው ዕለተ እሑድ፡ ቅዱስ ሥጋዋን ወስደው ቀብረውታል፡፡

እርሷም፡ በሦስተኛው ዕለት፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን፡ ማግሰኞ ተነሥታለች! የእመቤታችን ትንሣኤ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ"÷ ወይም፡ "እንደልጇ ትንሣኤ" ያሰኘው፡ ይህ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይታ የመነሣቷ እውነታ ነው፡፡

ይህም፡ "በገነት የቆየችው የእመቤታችን ቅድስት ነፍስ፡ በገነት አብሩዋት እንዲቆይ ተደርጎ፡ በሓዋርያት የሱባኤ ምልጃ ምክንያት፡ ኋላ፡ በመልአኩ እጅ፡ ወደምድር ተመልሶላቸው፡ እሑድ ቀብረውት፡ እስከማግሰኞ በመቃብር ካረፈው ቅዱስ ሥጋዋ ጋር፡ በሦስተኛው ቀን ተዋሕዳ፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች!" ማለት ነው:: በዚህም፡ ቀደም ብሎ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፥ መቃብርና ትንሣኤ ተፈጽሞ የታየው መለኮታዊ ትንግርት መደገሙ፡ በእውን ተረጋገጠ:: "መለኮት የተዋሓዳት፡ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ፡ በዕለተ ዓርብ፡ በመስቀል ላይ፡ ራቁቱን ከተዘረጋው ሥጋዋ ተለይታ፡ ያመኑ ነፍሳትን፡ ነጻ ልታወጣ፡ ወደሲዖል ወርዳ ሣለች፡ ያ በመስቀል ላይ ቀርቶ የነበረው፡ መለኮት የተዋሓደው ሥጋዋ ደግሞ፡ በመቃብር ዐርፎ፡ ከቆየ በኋላ፡ በሦስተኛው ቀን፡ እሑድ፡ ሥጋውና ነፍሱ እንደገና ተዋሕደው፡ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ" ማለት ነው::

ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ማለትም፡ በመጀመሪያው የሓዋርያት ሱባኤ ጊዜ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም:: ለሓዋርያት በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል፡ እርሱም፡ እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት ዘግይቶ፡ በዚያ እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሓዋርያት ሲመጣ፡ እመቤታችንን፡ ስታርግ አገኛት:: ያችም ዕለት፡ ትንሣኤዋ ብቻ ሳይኾን፡ ዕርገቷም፡ እንደልጇ ዕርገት፡ በ፵ኛው ቀን የተፈጸመባት፡ መስከረም ፳፩ ቀን፡ እሑድ ነበረች:: ቶማስም፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታወከበት።

ለእመቤታችንም፡ "ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቼ ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ፤ አኹን ደግሞ፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ይኸው፡ ያንቺን ትንሣኤ ቀድመው ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ!" ብሎ ማዘኑን ገለጸላት::

እመቤታችንም፡ "አይዞህ! አትዘን፤ እኒያ ወንድሞችህ፡ ኹላቸውም፡ ትንሣኤዬን፥ ዕርገቴንም አላዩም፤ አንተ ግን፡ ታድለሃል፤ ኹለቱንም አይተሃልና:: አኹንም፡ ኼደህ፡ 'ተነሣች! ዐረገች!' ብለህ ንገራቸው!" ብላ፡ ተገንዛበት የነበረውን ሰበን (ሽማ) ሰጥታ፡ ሰደደችው::

ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባኤና በጉባኤ የሰነበቱትን ሓዋርያትን ሲገናኛቸው፡ "ኧረ! የእመቤታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው:: እነርሱም፡ "ሥጋዋን ተቀብለንና አግኝተን ቀበርናት!" አሉት:: "መቼ?" አላቸው:: "በነሓሴ መባቻ ሱባኤ ገብተን፡ በ፲፮ኛው ቀን!" አሉት:: እርሱም፡ በመገረም፡ "ሞት በጥር፥ በነሓሴ መቃብር! ኧረ ተዉ! ይህ ነገር፡ አይመስለኝም!" አላቸው:: ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስም፡ "አንተ እንጃ፡ ልማድህ ነው! አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም፤ አንተ እየተጠራጠርህ፡ ሰውን ኹሉ፡ ስታጠራጥር ትኖራለህ፤ አኹንም፡ እውነቱን ልታውቅ ከወደድህ፡ ና! እይ!" አለው:: ቶማስም፡ የያዘውን ያውቃልና ፡ የቅዱስ ጴጥሮስን አነጋገር፡ ጸጥ ብሎ ሰምቶ ተከተለው::

ከዚህ በኋላ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ተቆጥቶ ኼዶ፡ መቃብሩን ቢከፍተው፡ አጣት፤ እርሱም፥ አብረውት የነበሩት የቀሩት ሐዋርያትም ደንግጠው በያሉበት ቆሙ። በዚህ ጊዜ፡ ቶማስ፡ "'አታምኑኝም!' ብዬ ነው እንጂ፡ እመቤታችንስ፡ ደስ ይበላችሁ! ተነሥታለች! ዐርጋለች!" አላቸው። ከእርሷ ያገኘውን፡ የተገነዘችበትንም ሰበን ሰጣቸው። ሐዋርያትም፡ ያን በማየታቸው፡ ደስ ብሏቸው፡ ለበረከት ተካፈሉት።

ይህ በኾነ፡ ልክ፡ በዓመቱ፡ የቀሩት ሐዋርያት፡ "ቶማስ፡ ትንሣኤሽን፥ ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? አቤቱ፡ እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተህ፡ አሳየን!" ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛ የሱባኤ ጾምንና ጸሎትን፡ ነሐሴ ፩ ቀን፡ በአንድነት ጀመሩ።

ነሐሴ ፲፬ ቀን፡ ኹለት ሱባኤን ጨርሰው፡ በሦስተኛው ዕለት፡ (ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው) ነሐሴ ፲፮ ቀን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ወደሰማያት ተነጥቀው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በጽርሓ አርያም፡ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ቄስ፥ ቅድስት እናቱን፡ እመቤታችንን ድንግል ማርያምን፡ መንበር፥ ቅዱስ ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፥ ቅዱስ እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ፡ ቆርቦ፥ እርሷንም፥ እነርሱንም፡ አቍርቧቸዋል።

\+ + +

"ፍልሰታ ለማርያም" በሚል ስያሜ፡ ነሐሴ ፲፮ ቀን ስለሚከበረው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የትንሣኤዋ መታሰቢያ ስለኾነው በዓለ ዕለት፡ ለማስረዳት፡ ከዚህ የሚከተለው ሐተታ፡ በጥቂቱም ቢኾን ቀርቧል።-

በዘመነ ፍጥረት፡ ዕፀ ሕይወት (የሕይወት ዛፍ)፥ በዘመነ አበው ደግሞ፡ የኖኅ መርከብ፥ በዘመነ ኦሪትም፡ የጽላተ ኪዳን ታቦት፡ ምሳሌዋ የኾነችው፡ የእግዚአብሔር ወልድ እናት፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ለመጨረሻው፥ ለኹለንተናዊውና ለዘለዓለማዊው ትንሣኤ፡ በኲር ከኾነው፡ ከልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥላ፡ በአዲስ ኪዳኑ የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይቶ የመነሣትን ክብር ያገኘች መኾኗን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በሃይማኖት የተቀበሉት እውነታ ነው።

በዚያች፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር በተቀበላት ጽላተ ኪዳን ላይ፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈው፡ ራሱ እግዚአብሔር ቃል፡ የተቀረጸባት ስትኾን፡ ያ የእግዚአብሔር ቃል፡ ጽላቷን፡ የራሱ አካል አድርጎ፡ በዘመነ ብሉይ፡ መለኮታዊ ክብሩን እንደገለጸባትና አምላካዊ ኃይሉን እንደፈጸመባት ኹሉ፥ ኋላም፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በዚያው ባሕርያዊ ጥበቡ፡ ከቅዱስ ሥጋዋ፡ ቅዱስ ሥጋን፥ ከቅድስት ነፍሷም፡ ቅድስት ነፍስን ነሥቶ፡ በተዋሐዳት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያን፡ በትንሣኤው እውንና ገሃድ ያደረገውን፡ አማናዊዉንና ዘለዓለማዊዉን ክብሩንና ኃይሉን፡ ለእርሷም አጐናጽፎ፡ እናቱን፡ ለፍጹሙ ሕያው ማንነት አብቅቷታል።

የዚህ እውነታ መነሻ፡ ድንግል ማርያም፡ “**ትፀንሲ!**”፡ ማለትም፡ “**ትፀንሻለሽ!**” ያላትን፡ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን የምሥራች ቃል ተቀብላ፡ “**ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ!**” ማለትም፡ “**እንዳልኸኝ (እንደቃልህ) ይኹንልኝ!**” ባለችበት ቅጽበት፡ “**ቃል ሥጋ ኾነ!**” ማለትም፡ “አምላክ ሰው ኾነ!” በሚለው የሥጋዌ ምሥጢር፡ የተፈጸመው ዕፁብ ድንቅ ተአምር ነው፡፡ የዚህ አማናዊ እውነታ መድረሻ ደግሞ፡ “**በሰማይም ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ! የኪዳኑም ታቦት፡ በመቅደሱ ታየ!**” በሚለው፡ በዮሓንስ ራእይ ተረጋግጦ እንደተነገረው፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ተሰጥታ ቆይታ፡ ኋላ፡ ወደኢትዮጵያውያን ተዛውራና በአደራ ተጠብቃ የኖረችው ታቦተ ጽዮን፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ወደሰማያት ተመልሳ በምትገኝበት ህልውናዋ የተገለጠው፡ ሌላው፡ ዕፁብ ድንቅ ተአምር ነው፡፡ (ሉቃ. ፩÷ ፳፮-፴፰፡፡ ዮሓ. ፩÷ ፲፬፡፡ ራእ. ፲፩÷ ፲፱፤ ፲፪፡፡)

ይህን ታላቅ ትንግርታዊ ቊም ነገር፡ እንዲህ በሚል ጥቂት ቃል፡ ልናጠቃልለው ይቻላል፤ ይኸውም፡-

በቅድሚያ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢርና ጥበብ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ዐርፎ የተፀነሰው፡ ያው፡ በጽላቷ ላይ ተቀርጾ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ÷

ቀጥሎ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ ኪዳንና የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው፡ የጽላቷ ማደሪያ ታቦት (ሣጥን)፡ ኹለቱም፡ በምድር ላይ ከነበሩበት ግዙፍ ህልውናቸው ተሠውረው፡ በሰውነት መገለጻቸው÷

በመጨረሻም፡ በሕይወተ ሥጋ ኖረው÷ ተልእኳቸውንም ፈጽመው፡ በአዲሱ ኪዳን የትንሣኤ አካል፡ ከሙታን ተለይተው ከተነሡ በኋላ፡ በዚያ ሕያው አካላቸው፡ ወደሰማይ ዐርገው፡ ዛሬ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በሰማይና በምድር በሰፈነችው በዘለዓለማዊቷ መንግሥታቸው ነግሠውና በሰማያዊው ዙፋናቸው ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መኾናቸው ነው፡፡

የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሃይማኖትነቷና የመቅደስነቷ÷ የእመቤትነቷና የኪዳንነቷ÷ የእናትነቷና የአገርነቷ÷ የንግሥትነቷም ፍቅር፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እጅግ የጠለቀና የመጠቀ በመኾኑ፡ ቅዱሳን ሓዋርያት፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ባላቸው ፍቅር፡ በጾም÷ በጸሎትና በምጽዋት (በበጎ ምግባር) ተጠምደው፡ ኹለት ጊዜያት ያካኼዱትን፡ ይህን የኹለት ሳምንታት ሱባኤ፡ እኒሁ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚሁ መልክ፡ ለኹለት ሳምንታት፡ በሱባኤ ተወስነው የሚፈጽሙት፡ በዚህ ምክንያት ነው፡፡

በጥር ፳፩ ቀን፡ በዕረፍተ *ሥጋዋና* በፍልሰተ *ሥጋዋ* ተጀምሮ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን የተፈጸመው፡ ይህ፡ የትንሣኤ በዓሏ፡ “ከመ ትንሣኤ ወልዳ!” ማለትም፡ “እንደልጅዋ ትንሣኤ ስለኾነ፡ እንደልጇ ትንሣኤ በዓል አድርገው ያክብሩት!” ሲሉ፡ የቀደሙት ወላጆቻቸው የደነገጉትን ተከትለው፡ እንደልጇ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በታላቅ ሓሤትና ይባቤ ያከብሩታል።

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚህ በዓላቸው ዕለትና ወራት፡ የሚሰማቸው ደስታ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻለውን፡ በልጇ የትንሣኤ በዓል ጊዜ የሚሰማቸውን ይመስላል፤ ይኸውም፡ ከነሓሴ ፲፮ እስከ፴ ቀን ድረስ፡ በፋሲካ ስሜትና ዝግጅት፡ የሚያሳልፉት በመኾኑ ነው። ይህ የተመስጦ ስሜታቸውና ዝግጅታቸው፡ ከሚገለጽባቸውና እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልባችን ከጻፋቸው፡ የማኅሌትና የመዝሙር በረከቶቻቸው መካከል፡ *“ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! ተፈጸመ ትንሣኤሃ፥ ወዕርገታ ዘልዑል!”* እያሉ የሚያቀርቡት ዝማሬ ይገኛል፤ የዚህም ትርጉም፡ “የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው፡ የድንግል ማርያም ትንሣኤና ዕርገቷ፡ እንደልዑል አምላክ ልጇ ትንሣኤና ዕርገት፡ እውን ኾኖ ተፈጸመ!” የሚል ነው። የዕርገቷንም በዓል፡ በዚሁ መልክ፡ በመስከረም ፳፩ ቀን ያከብሩታል።

ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብአዊ ፍጡሩ ዐቅዶ ያዘጋጀው የቸርነት ሥራው፡ ለመጨረሻው ዘውድ የበቃ መኾኑ፡ በእርሷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም የተረጋገጠበት፡ የዚህ ዕፁብ ድንቅ ተአምሩ ዜና፡ በየጊዜያቱና በየቦታው፥ በየምክንያቱም የሚነገር ከመኾኑ ጋር፡ እኒሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚያ በዓላቸው ላይ፡ *“ተንሥአት እሙታን፡ ማርያም ድንግል! ከመ ትንሣኤ ወልዳ ዘልዑል!”* ማለትም፡ “ድንግል ማርያም፡ ከሙታን ተለይታ ተነሣች! በሉዓላዊው የልጇ ትንሣኤ፡ እርሱን መሰለች!” የሚለውን የምሥራች ቃል፡ በታላቅ ሓሤት ይለዋወጣሉ።

ይህ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ የልጇ፡ የበዓለ ትንሣኤው ወራት፡ የረቡዕና የዓርብ ጾም ሳይኖርበት፡ እስከበዓለ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ ለአምሳ ቀናት ተራዝሞ፡ እንደሚከበር ኹሉ፡ የእርሷም፡ የትንሣኤ በዓሏ፡ በእኒሁ ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ ዘንድ፡ በዚሁ መልክና ሥርዓት፡ እስከነሓሴ ፴ ቀን ድረስ መከበሩ ይቀጥላል።

እንግዴህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የአዲሱ ዓመት መግቢያና መነሻ ዐውደ ዓመት፥ የቅድስት ድንግል ማርያምና የልጇ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት፥ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ የነጻነት በዓል ከኾነው፡ ከመስከረም ፩ ቀን በፊት፡ የዘመኑ የመጨረሻ ታላቅ በዓላችን አድርገን፡ በየዓመቱ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ በያለንበት የምንዘክረውን፡ ይህን፡ የበዓለ ትንሣኤ ለማርያምን በዓል፡ በምን ዓይነት የተመስጦ ስሜት ልናከብረው እንደሚገባን፡ አስቀድመን አውቀነው፡ ልንዘጋጅበት ያስፈልገናል።

ለነሓሴ ፲፮ አጥቢያ ሌሊት፡ የምንፈጽመው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ዮሓንስ፡ በራእዩ ያየውን፡ ያን፡ የሰማዩን ሥርዓት፡ በምድርም ላይ እውን አድርገን፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ምድራዊትና ሰማያዊት መቅደሱ በኾነችው፡ በቅድስት ንግሥት እናቱ፡ በድንግል ማርያም መንበርነትና ታቦትነት ቀድሶ፡ ሓዋርያትን እንዳቆረበ፥ እንዲሁ፡ እኛም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ ኢትዮጵያ፡ ዕለቲቱን በማዘከር፡ በኢትዮጵያዊቷ ምድራዊት መቅደሱ፡ ያንኑ ሰማያዊ ሥርዓት፡ ማለትም፡ <u>ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በመቀበል</u>፡ መልሰን መፈጸማችን መኾኑን ማመን ይገባናል።

## ጾመ ጳጉሜ።

"ጾመ ፍልሰታ" ካበቃች በኋላ፡ ኹለት ሳምንቶችን፡ በሥጋዊውና መንፈሳዊው የፋሲካ ደስታና የሓሤት ድግሥ ቆይተን፡ "ጾመ ጳጉሜ"፥ ወይም፡ "የጳጉሜ ጾም" ተብላ፡ ከሌሎቹ፡ የዓመቱ አጽዋማታችን መካከል፡ አንዲቱ ኾና የምታስተናግደን ሰሞን ትቀበለናለች። እርሷም፡ በመስከረም ፩ ቀን ለሚውለው፡ ለታላቁ የዐውደ ዓመት በዓላችን፡ ሰሙነ ዋዜማ የኾነችው የዓመቱ መደምደሚያ ጾም ናት ።

ጳጉሜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም የልደታት ቀን፡ እንደጾመ ገሃድ፥ አዲሱንም ዓመተ ምሕረት፡ በንስሓ ተዘጋጅተው ሊሸጋገሩባት፡ ሰሙነ ሱባኤ ኾና፡ ስትጾም የኖረች በመኾኗ፡ ዛሬም፡ እኛ፡ የአኹኖቹ ልጆቻቸው፡ በዚሁ መልክ የምንመራባትና የምንገለገልባት፥ የምንጠቀምባትም ኾናልናለች።

አዎን! መስከረም ፩ ቀን፡ ክፉዉን ኹሉ፡ ካረጀው ዓመት ጋር፡ ከወዲሁ ጥለንና ትተን፥ አስወግደንና አጥድተንም፥ የእየራሳችንን ኹለንተና፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት፡ በንስሓ አድሰን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ እንደአዲስ ተሸላሚ፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል ተቀብለን፡ የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት፡ ቅድስት ዕለት ናት።

ከዚህ የተነሣ፡ የጌታችንና የእመቤታችን የልደት በዓላት የሚውሉባትን፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ እውነተኛና ተገቢ በኾነው፡ የአምልኮ መንፈስ ለማክበር፡ ነፍሳችንንና ሥጋችንን፥ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን፡ ሰውነታችንን፡ እንዲህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሕይወት የምናበቃባት፥ በአገርነትና በመንግሥትነት፡ የነጻነት በዓሏን፡ በዚያች ዕለት ለምናከብርላት፡ “ኢትዮጵያ” ለተባለችው፡ እናቱና እናታችንም፡ “ዕንቍጣጣሽ! (እነሆ፡ ዕንቍ ለጣትሽ!)” ብለን፡ የደስታና የምስጋና ገጸ በረከትን የምናቀርብባት፥ እርስ በርሳችንም፡ የአበባ ነዶና ጕንጕን አዘጋጅተን፡ “የምሥራች! እንኳን አሸጋገረን! እንኳን አደረሰን!” እያልን፡ መልካም ምኞታችንን የምንለዋወጥባት፡ የተመረጠች፡ የእግዚአብሔር ቀን መኾኗን አውቀን፡ ከወዲሁ፡ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ይገባናል።

በዚህ መልክ የምንዘጋጅባትንና ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን፡ ይህችኑ ጳጕሜን፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያ ንና ኢትዮጵያውያት፡ ንዑስ ሱባኤ አድርገን፡ እነሆ፡ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት ልናሳልፋት፡ በጉጉት እንጠብቃታለን።

\+ + +